| ነገድ | ብዛት |
|---|---|
| የሮቤል | 46,500 |
| የስምዖን | 59,300 |
| የጋድ | 45,650 |
| የይሁዳ | 74,600 |
| የይሳኮር | 54,400 |
| የዛብሎን | 57,400 |
| የኤፍሬም | 40,500 |
| የምናሴ | 32,200 |
| የብንያም | 35,400 |
| የዳን | 62,700 |
| የአሴር | 41,500 |
| የንፍታሌም | 53,400 |
| በድምሩ | 603,550 |

47 ሌዋውያን ግን ከሌሎች ነገዶች ጋር
እብረው አልተመዘገቡም ፤ 48 ምክንያቱም እግ
ዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎት ስለነበር
ነው ፦ 49 “ወታደር ሆነው ማገልገል የሚችሉ
ትን ወንዶች ስትቈጥር ፥ የሌዊን ነገድ አት
ጨምር ። 50 በዚህ ፈንታ ሌዋውያንን እኔ በም
መለክበት ድንኳንና በውስጡም ባሉት የመገ
ልገያ ዕቃዎች ላይ ኀላፊዎች አድርገህ መድ
ባቸው ፤ እነርሱ ድንኳኑንና በውስጡ ያሉትን
የመገልገያ ዕቃዎች ሁሉ ይሸከማሉ ፤ በድንኳ
ኑም ውስጥ ያገለግላሉ ፤ በዙሪያውም ይሰፍ
ራሉ ። 51 ሰፈራችሁን ለቅቃችሁ በምትሄዱበት
ጊዜ ፥ ሌዋውያን ብቻ ድንኳኑን ነቅለው በሚ
ሰፍሩበት አዲስ ቦታ ይተክሉታል ፤ ከእነርሱ
በቀር ወደ ድንኳኑ የሚቀርብ ማንኛውም
ሰው በሞት ይቀጣል ። 52 ሌሎቹ እስራኤላው
ያን እያንዳንዱ የመለያ ዓርማውን ይዞ በቡ
ድን በቡድን በመከፋፈል ለየብቻው ይሰፍ
ራል ። 53 ነገር ግን ማንም ሰው ወደ ድንኳኑ
በመቅረብ ቍጣዬን እንዳያመጣ የእስራኤልን
ማኅበር እንዳያስፈጅ ሌዋውያን በድንኳኑ
ዙሪያ ሰፍረው ይጠብቁት ።” 54 ስለዚህ የእስ
ራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው
መሠረት ሁሉን ነገር አደረጉ ።

## ምዕራፍ 2
### የነገዶች ሰፈር አመዳደብ

1 እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን የሚከተለ
ውን መመሪያ ሰጣቸው ፤ 2 እስራኤላውያን በሚ
ሰፍሩበት ቦታ ሁሉ እያንዳንዱ ሰው ክፍሉ ተለ
ይቶ የሚታወቅበትን ዓርማ ተከትሎ በየነገዱ
ሰንደቅ ዓላማ ሥር ይሰፍራል ፤ ሰፈሩም
በድንኳኑ ዙሪያ ይሆናል ።
3-9 በስተ ምሥራቅ ፥ በይሁዳ ክፍል ዓርማ
ሥር የተጠቃለሉት ሦስቱ ነገዶች በየምድብ
ቦታቸው ይሰፍራሉ ፤ የየነገዱ የቤተሰብ አለቆ
ችም የሚከተሉት ናቸው ፦

| ነገድ | አለቃ | ብዛት |
|---|---|---|
| የይሁዳ | የዓሚናዳብ ልጅ ነአሶን | 74,600 |
| የይሳኮር | የጹዓር ልጅ ናታንኤል | 54,400 |
| የዛብሎን | የሔሎን ልጅ ኤሊአብ | 57,400 |

የእነርሱም ጠቅላላ ድምር 186,400 ነበር ።

በዚህ ዐይነት የይሁዳ ክፍል በመጀመሪያ
ይጓዛል ።
10-16 በስተ ደቡብ በኩል በሮቤል ክፍል
ዓርማ ሥር የተጠቃለሉት ሦስቱ ነገዶች በየም
ድብ ቦታቸው ይሰፍራሉ ፤ የየነገዱ የቤተሰብ
አለቆችም የሚከተሉት ናቸው ፦

| ነገድ | አለቃ | ብዛት |
|---|---|---|
| የሮቤል | የሸዲኡር ልጅ ኤሊጹር | 46,500 |
| የስምዖን | የጹሪሻዳይ ልጅ ሸሉሚኤል | 59,300 |
| የጋድ | የደዑኤል ልጅ ኤልያሳፍ | 45,650 |

የእነርሱም ጠቅላላ ድምር 151,450 ነበር ።

በዚህ ዐይነት የሮቤል ክፍል በሁለተኛ
ደረጃ ይጓዛል ።
17 በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎችና በመ
ጨረሻዎቹ ሁለት ክፍሎች መካከል ሌዋውያን
ድንኳኑን ይዘው ይጓዛሉ ፤ እያንዳንዱም ክፍል
ሰፈሩ ተለይቶ በሚታወቅበት ዓርማ ሥር
ምድብ ተራውን ጠብቆ ይጓዛል ።
18-24 በስተምዕራብ በኩል በኤፍሬም ክፍል
ዓርማ ሥር የተጠቃለሉት ሦስት ነገዶች በየም
ድብ ቦታቸው ይሰፍራሉ ፤ የየነገዱ የቤተሰብ
አለቆችም የሚከተሉት ናቸው ፤

| ነገድ | አለቃ | ብዛት |
|---|---|---|
| የኤፍሬም | የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሻማዕ | 40,500 |
| የምናሴ | የፕዳጹር ልጅ ገማልኤል | 32,200 |
| የብንያም | የጊድዖኒ ልጅ አቢዳን | 35,400 |

የእነርሱም ጠቅላላ ድምር 108,100 ነበር ።

በዚህ ዐይነት የኤፍሬም ክፍል በሦስተኛ
ደረጃ ይጓዛል ።
25-31 በስተ ሰሜን በኩል በዳን ክፍል ዓርማ
ሥር የተጠቃለሉት ሦስት ነገዶች በየምድብ
ቦታቸው ይሰፍራሉ ፤ የየነገዱ የቤተሰብ አለቆ
ችም የሚከተሉት ናቸው ።

| ነገድ | አለቃ | ብዛት |
|---|---|---|
| የዳን | የዓሚሻዳይ ልጅ አሒዔዘር | 62,700 |
| የአሴር | የዖክራን ልጅ ፋግዒኤል | 41,500 |
| የንፍታሌም | የዔናን ልጅ አሒራዕ | 53,400 |

የእነርሱም ጠቅላላ ድምር 157,600 ነበር ።

በዚህ ዐይነት የዳን ክፍል በአራተኛ ደረጃ
ይጓዛል ።
32 በየክፍሉ ተመድበው የተመዘገቡት የእስ
ራኤል ሕዝብ ጠቅላላ ድምር 603,550

ነበር ። 33 ሌዋውያን ግን እግዚአብሔር ሙሴን
ባዘዘው መሠረት ፥ ከሌሎቹ የእስራኤል ሕዝብ
ጋር አልተመዘገቡም ።
34 በዚህ ዐይነት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአ
ብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ሁሉን ነገር
ፈጸሙ ፤ እያንዳንዱ ነገድ ዓርማውን በመከተል
ይሰፍር ነበር ፤ እያንዳንዱም በየቤተሰቡ ተመ
ድቦ ይጓዝ ነበር ።

## ምዕራፍ 3

### የአሮን ወንዶች ልጆች

1 እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ ላይ
ባነጋገረው ጊዜ የአሮንና የሙሴ ቤተሰብ ይህ
ነበር ። 2 አሮን አራት ወንዶች ልጆች ሲኖሩት
እነርሱም በኵሩ ናዳብ ፥ አቢሁ ፥ አልዓዛርና
ኢታማር ነበሩ ። 3 ሁሉም ተቀብተው የክህነት
ማዕርግ ተቀበሉ ፥ 4 ነገር ግን ከእነርሱ ውስጥ
ናዳብና አቢሁ በሲና በረሓ ያልተቀደሰ እሳት
ጭረው ለእግዚአብሔር በማቅረባቸው ተቀሥ
ፈው ሞቱ ፤ እነርሱም ልጆች አልነበሩአቸ
ውም ፤ ስለዚህም አልዓዛርና ኢታማር ብቻ
አሮን በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ በክህነት
ያገለግሉ ነበር ።

### ሌዋውያን ካህናትን እንዲያገለግሉ ተመደቡ

5 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
6 "የሌዊን ነገድ አቅርበህ ለካህኑ አሮን ረዳቶች
አገልጋዮች እንዲሆኑ መድባቸው ፤ 7 እነርሱ
እኔ በምመለከበት ድንኳን ማንኛውንም ሥራ
ይፈጽሙ ፤ እንዲሁም ስካህናቱና ለመላው
ማኅበር ልዩ ልዩ ሥራዎችን ያከናውናሉ ።
8 በድንኳኑ ውስጥ መገልገያ ለሆኑት ዕቃዎች
ሁሉ ኀላፊዎች ይሆናሉ ፤ የሌሎቹን እስራኤላ
ውያን የሥራ ድርሻ ሁሉ እነርሱ ያከናውናሉ ።
9 ስለዚህም የሌዋውያን ኀላፊነት አሮንንና ልጆ
ቹን በመርዳት ማገልገል ይሆናል ። 10 የክህነቱ
ንም ሥራ ያከናውኑ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን
ሹማቸው ፤ ከእነርሱ በቀር ሌላ ሰው ይህን
ሥራ ለማከናወን ቢሞክር በሞት ይቀጣ ።"
11 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
12-13 "እነሆ ሌዋውያን የእኔ አገልጋዮች
ናቸው ፤ የግብጻውያንን በኵር ሁሉ በገደልሁ
ጊዜ ከእያንዳንዱ እስራኤላዊ የሚወለደውን
በኵርና ከእንስሳቱም በኵር የሆነውን ሁሉ
ለእኔ የተለየ እንዲሆን አድርጌ ነበር ፤ አሁን
ግን በኵር ሆነው የሚወለዱትን ወንዶች ልጆች
የራሴ አድርጌ በመለየት ፈንታ ሌዋውያንን
መርጫለሁ ፤ እነርሱ የእኔ አገልጋዮች ይሆ
ናሉ ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ።"

### የሌዋውያን መቈጠር

14 እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ ላይ
እንዲህ ሲል አዘዘው ፥ 15 "ሌዋውያንን በየወገና
ቸውና በየቤተሰባቸው መድበህ ቍጠር ፤ ከተወ
ለደ አንድ ወር የሞላው ወይም ከዚያ በላይ
የሆነውን ወንድ ሁሉ መዝግብ ።" 16 ሙሴም
እንዲሁ አደረገ ፤ 17-20 ሌዊ ሦስት ወንዶች
ልጆች ነበሩት ፤ እነርሱም ጌርሾን ፥ ቀሃትና
መራሪ ተብለው ይጠራሉ ፤ በየስማቸውም የቤ
ተሰብ አባቶች ነበሩ ። ጌርሾንም ሊብኒና
ሺምዒ የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት ፤
ቀሃትም ዓምራም ፥ ይጽሃር ፥ ኬብሮንና ዑዚ
ኤል የተባሉ አራት ወንዶች ልጆች ነበሩት ፤
መራሪም ማሕሊና ሙሺ የተባሉ ሁለት ወን
ዶች ልጆች ነበሩት ፤ እነዚህም ሁሉ በየስማ
ቸው የቤተሰብ አባቶች ነበሩ ።
21 የሊብኒና የሺምዒ ቤተሰቦች በጌርሾን
ጐሳ ውስጥ ተጠቃለው ነበር ፤ 22 በዚህ ዐይነት
ዕድሜው አንድ ወር ከሆነው ሕፃን አንሥቶ
የተመዘገቡት የወንዶች ብዛት ሰባት ሺ አምስት
መቶ ነበር ። 23 ይህም ጐሳ የሚሰፍረው
በድንኳኑ በስተጀርባ በምዕራብ በኩል ነበር ።
24 የዚያም ጐሳ አለቃ የላኤል ልጅ የሆነው
ኤልያሳፍ ነበረ ። 25 የእነርሱም ኀላፊነት
በድንኳኑ ከውስጥና ከውጭ በኩል ባለው መሸ
ፈኛ ፥ በመግቢያው ደጃፍ መጋረጃ ፥ 26 በድንኳ
ኑና በመሠዊያው ዙሪያ በሚገኙት መጋረጃ
ዎች ፥ ወደ አደባባዩ በሚያስገባው ደጃፍ በሚ
ገኘው መጋረጃ ላይ ሲሆን ፥ በአጠቃላይ እነዚ
ህን ነገሮች በሚመለከት ሥራ ኀላፊነቱ የእነ
ርሱ ነበር ።
27 የዓምራም ፥ የይጽሃር ፥ የኬብሮንና የዑዚ
ኤል ቤተሰቦች በቀሃት ጐሳ ውስጥ ተጠቃለው
ነበር ፤ 28 በዚህ ዐይነት ዕድሜው አንድ ወር
ከሆነው ሕፃን አንሥቶ የተመዘገቡት የወንዶች
ብዛት ስምንት ሺ ስድስት መቶ ነበር ።
29 ይህም ጐሳ የሚሰፍረው በድንኳኑ በስተደ
ቡብ በኩል ነበር ። 30 የቀሃትም ጐሳ አለቃ የዑ
ዚኤል ልጅ የሆነው ኤሊጻፋን ነበር ። 31 የእነር
ሱም ኀላፊነት በቃል ኪዳኑ ታቦት ፥ በገበ
ታው ፥ በመቅረዙ ፥ በመሠዊያዎቹ ፥ ካህናቱ
በተቀደሰው ስፍራ በሚገለገሉባቸው ንዋያተ
ቅድሳት ፥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚያስገባው
መጋረጃ ላይ ሲሆን ፥ በአጠቃላይ እነዚህን ነገ
ሮች በሚመለከት ሥራ ኀላፊነቱ የእነርሱ
ነበር ።
32 የሌዋውያን ሁሉ አለቃ የካህኑ የአሮን
ልጅ አልዓዛር ነበር ፤ እርሱ በተቀደሰው ስፍራ
ለሚያገለግሉት ሰዎች ሁሉ የበላይ ኀላፊ
ነበር ።

3፡2 ፦ ዘኍ. 26፡60 ። 3፡4 ፦ ዘሌ. 10፡1-2 ፤ ዘኍ. 26፡61 ። 3፡13 ፦ ዘጸ. 13፡2 ።

ሆነ ዘቢብ አይብላ ፤ 4 በናዝራዊነቱ ወቅት ከወ
ይን ሐረግ የሚገኘውን ሁሉ ፥ የወይኑን ፍሬ
ግልፋፊ ወይም ዘር አይብላ ።

5 "ስእለት ተስሎ በናዝራዊነት እስካለ ድረስ
ጠጕሩን መላጨትም ሆነ መቍረጥ የለበትም ፤
የናዝራዊነት ጊዜው እስኪፈጸም ድረስ ለእግዚ
አብሔር የተለየ ይሆናል ፤ ጠጕሩንና ጢሙንም
ያሳድጋል ። 6-7 ጠጕሩን ማሳደጉ ለእግዚአብ
ሔር የተለየ ለመሆኑ ምልክት ነው ፤ ስለዚህ
ወደ ሞተ ሰው ሬሳ በመቅረብ ራሱን አያርክስ ፤
አባቱም ሆነ እናቱ ፥ ወንድሙም ሆነ እኅቱ
ቢሞቱ ሬሳቸውን አይንካ ። 8 ናዝራዊ እስከሆነ
ድረስ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው ።

9 "የአንድ ናዝራዊ የተቀደሰ ጠጕር ድንገት
ወደ ሞተ ሰው ሬሳ በመቅረቡ ምክንያት ቢረ
ክስ ፥ ለሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ጠጕሩንና
ጢሙን ይላጭ ፤ በዚህም ዐይነት በሕጉ መሠ
ረት በሥርዓት የነጻ ይሆናል ። 10 በሰምንተኛው
ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት ርግቦች እግዚ
አብሔር በሚመለክበት ድንኳን ደጃፍ ወደሚገ
ኘው ካህን ያምጣ ። 11 ካህኑም አንዱን ስለ
ኃጢአት ስርየት መሥዋዕት ፥ ሌላውን የሚቃ
ጠል መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ናዝራዊው
ሬሳ በመንካቱ ስለረከሰ ፥ የመንጻትን ሥርዓት
ይፈጽምለታል ፤ በዚያኑ ቀን ናዝራዊው ጠጕሩን
እንደገና ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ያደርገዋል ።
12 በናዝራዊነትም ለማገልገል ራሱን እንደገና
ለእግዚአብሔር የተለየ ያደርጋል ፤ ለእግዚአብ
ሔር የተቀደሰው ጠጕሩ ከመርከሱ የተነሣ
ከዚያ በፊት በናዝራዊነት የነበረበት ክፍለ ጊዜ
አይቈጠርለትም ፤ ስለበደልም ለሚከፈለው ዋጋ
አንድ ዓመት የሞላው የበግ ጥቦት ያምጣ ።

13 "አንድ ናዝራዊ ስእለቱን ሲጨርስ የሚፈ
ጽመውም ሥርዓት ይህ ነው ፦ ወደ ድንኳኑ
መግቢያ በር ሄዶ ፥ 14 ምንም ነውር የሌለባቸ
ውን ሦስት እንስሳት መሥዋዕት በማድረግ ለእ
ግዚአብሔር ያቀርባል ፤ ይኸውም ለሚቃጠል
መሥዋዕት አንድ ዓመት የሞላው የበግ ጥቦት ፥
ስለ ኃጢአት ስርየት ለሚቀርበውም መሥዋዕት
አንድ ዓመት የሞላት እንሰት የበግ ጥቦት ፥ እን
ዲሁም ስለ ደኅንነት የሚቀርብ የኅብረት መሥ
ዋዕት አንድ አውራ በግ ያቀርባል ማለት ነው ።
15 ደግሞም እርሾ ሳይነካው የተጋገረ አንድ
መሶብ እንጀራ ፥ በወይራ ዘይት ከተለወሰ
ዱቄት የተጋገረ ውፍረት ያለው ኅብስት ፥ በወ
ይራ ዘይት የተቀቡ ስስ ቂጣዎች ጭምር ዘወ
ትር ከሚቀርበው ከእህል ቍርባንና ከወይን
ጠጅ መባ ጋር አብሮ ይቅረብ ።

16 "ካህኑ ይህን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመሠ
ዋት ስለ ኃጢአት ስርየት መሥዋዕትና የሚቃ
ጠልን መሥዋዕት ያቀርባል ። 17 አውራውን
በግ ስለ ደኅንነት የሚቀርብ የኅብረት መሥዋ
ዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀርበዋል ፤ እርሱ
ንም በመሶብ ካለው እንጀራ ጋር ያቀርበዋል ፤
ቀጥሎም የእህሉን ቍርባንና የወይን ጠጁን
መባ ያቀርባል ። 18 በድንኳኑ በር መግቢያ ላይ
ናዝራዊው ጠጕሩን ላጭቶ ስለ ደኅንነት የሚቀ
ርበው የኅብረት መሥዋዕት በሚቃጠልበት
እሳት ላይ ያኖረዋል ።

19 "የአውራው በግ ወርች ከተቀቀለም በኋላ
ካህኑ ወርቹን በመሶቡ ካለው አንድ ወፍራም
ኅብስትና አንድ ስስ ቂጣ ጋር ወስዶ ናዝራዊ
በሆነው ሰው እጆች ላይ ያኖረዋል ፤ 20 ከዚህም
በኋላ ካህኑ ይህን ሁሉ ወስዶ ለእግዚአብሔር
የሚወዘወዝ ልዩ መባ አድርጎ ያቀርበዋል ፤
ይህም ሁሉ በሕጉ መሠረት የካህኑ ድርሻ ሆኖ
ከሚነሣው ከአውራው በግ ፍርንባና ወርች ጋር
ለካህኑ የተቀደሰ ድርሻ ይሆናል ፤ ናዝራዊው
የወይን ጠጅ መጠጣት የሚፈቀድለትም ከዚያን
በኋላ ነው ።

21 "እንግዲህ እነዚህ ስለ ናዝራዊያን የተሰጡ
የሥርዓት መመሪያዎች ናቸው ፤ ነገር ግን አንድ
ናዝራዊ በስእለቱ መሠረት ሊያቀርብ ከሚገባው
በላይ ለመስጠት ቃል ቢገባ ፥ በገባው ቃል መሠ
ረት ስእለቱን መፈጸም አለበት ።"

### የካህናት ቃለ ቡራኬ

22 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል አዘ
ዘው ፥ 23 "አሮንና ልጆቹ የእስራኤልን ሕዝብ
በሚባርኩበት ጊዜ እንዲህ በሉ ብለህ ንገራ
ቸው ፦

24 'እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም ፤
25 እግዚአብሔር የፊቱን ብርሃን
ይግለጥልህ ፥ ይራራልህም ፤
26 እግዚአብሔር በምሕረት ዐይን
ይመልከትህ ፤
ሰላሙንም ይስጥህ ።' "

27 ደግሞም እግዚአብሔር "በዚህ ሁኔታ
ስሜን ጠርተው የእስራኤልን ሕዝብ ቢባርኩ ፥
እኔም እነርሱን እባርካቸዋለሁ" አለው ።

## ምዕራፍ 7

### የሕዝቡ አለቆች ያቀረቡት ስጦታ

1 ሙሴ እግዚአብሔር የሚመለክበትን
ድንኳን ተክሎ በፈጸመበት ቀን ድንኳኑንና
የመገልገያ ዕቃዎቹን ፥ መሠዊያውንና የመገል
ገያ ዕቃዎቹን ፥ ዘይት በመቀባት ቀደሳቸው ፤
2 ከዚያን በኋላ በእስራኤል ነገዶች መካከል
የጐሳ አለቆች የሆኑት ፥ ማለትም በሕዝብ
ቈጠራ ጊዜ ኀላፊነት የነበራቸው ሁሉ ፥ 3 መባ
ቸውን ለእግዚአብሔር አቀረቡ ፤ ያቀረቡአቸ
ውም መባዎች በየሁለቱ አለቆች ስም አንድ

6፥13-21 ፦ ሐ.ሥ. 21፥23-24 ።

8-9 እርሱም በሰፈር ውስጥ በሌሊት ረግፎ ከጤዛ
ጋር ይገኝ ነበር ፤ በማግሥቱ ጠዋት ሕዝቡ በየ
ስፍራው ተዘዋውረው ከለቀሙት በኋላ በመው
ቀጥ ወይም በመፍጨት እንደ ዱቄት ያደቁ
ታል ፤ ከዚያም በኋላ ቀቅለው እንደ እንጎቻ
አድርገው ይጋግሩታል ፤ ጣዕሙም በዘይት ተለ
ውሶ እንደተጋገረ ቂጣ ነበር ።)
10 ሕዝቡ ሁሉ በየድንኳኖቻቸው ደጃፍ ላይ
በቡድን በቡድን ቆመው ሲያጕረመርሙ ሙሴ
ሰማቸው ፤ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ተቈጥቶ
ስለነበረ በጣም ተጨነቀ ። 11 እግዚአብሔርንም
እንዲህ አለው ፤ "ይህን ከባድ ነገር በእኔ በአገ
ልጋይህ ላይ ስለምን አመጣህብኝ? በእኔስ የማ
ትደሰተው ስለምንድን ነው? በዚህስ ሁሉ
ሕዝብ ላይ ይህን ያህል ከባድ ኀላፊነት ስለምን
ሰጠኸኝ? 12 እኔ አልፈጠርሁአቸውም! ወይም
እምጬ የወለድሁአቸው አይደሉም! ታዲያ
ለቀድሞ አባቶቻቸው ልትሰጣቸው ቃል ወደገባ
ህላቸው ምድር እስኪገቡ ድረስ ፤ ለዚህ ሁሉ
ሕዝብ ሞግዚት በመሆን እንደ ሕፃናት ተሸክ
ሜአቸው እንድጓዝ ያደረግኸው ስለምንድን
ነው? 13 እንግዲህ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ
ሥጋ ከወዴት አገኛለሁ? እነርሱ የሚበሉት
ሥጋ ለማግኘት ያላቸው ፍላጎት እጅግ የበረታ
ነው ፤ 14 እኔ ይህን ሁሉ ሕዝብ ብቻዬን መም
ራት አልችልም ፤ ይህ ኀላፊነት ለእኔ እጅግ
ከባድ ነው! 15 በዚህ ሁኔታ እንድሠቃይ ከምታ
ደርገኝ ይልቅ ብትራራልኝና አሁኑኑ ብትገድ
ለኝ ይሻላል ፤ ከዚያም በኋላ አንተ ከምታመጣ
ብኝ መከራ እገላገላለሁ ።"
16 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤
"ለሕዝብ አመራር በመስጠት የታወቁ ሰባ ሰዎ
ችን ምረጥ ፤ እነርሱንም ሰብስበህ እኔ ወደምመ
ለክበት ድንኳን አምጣቸውና በአጠገብህ
ይቁሙ ፤ 17 እኔም ወደዚያ ወርጄ ከአንተ ጋር
እነጋገራለሁ ፤ ለአንተም ከሰጠሁህ መንፈስ
ከፍዬ ለእነርሱ እሰጣቸዋለሁ ፤ ከዚያም በኋላ
በእነዚህ ሕዝብ ላይ ያለህን ኀላፊነት በመሸከም
ይረዱሃል ፤ ከእንግዲህም ወዲህ ይህን ሁሉ ኀላ
ፊነት ብቻህን አትሸከምም ። 18 አሁንም ለሕ
ዝቡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው ፤ 'ለነገ ራሳችሁን
አንጹ ፤ የምትበሉትም ሥጋ ይኖራችኋል ፤
ሥጋ ለማግኘት በብርቱ መመኘታችሁንና ይል
ቁንም በግብጽ ምድር በመልካም ትኖሩ እንደነ
በር በማጕረምረም መናገራችሁን እግዚአብሔር
ሰምቶአል ፤ እነሆ አሁን እግዚአብሔር ሥጋ
ይሰጣችኋል ፤ እርሱንም እስክትጠግቡ ትበላላ
ችሁ ። 19 የምትበሉትም ለአንድ ወይም ለሁለት
ቀን ለአምስት ፤ ለዐሥር ወይም ለሃያ ቀን ብቻ
አይደለም ፤ 20 እስኪያንገፈግፋችሁና በአፍንጫ
ችሁ እስኪወጣ ድረስ አንድ ወር ሙሉ ትመገ
ቡታላችሁ ፤ ይህም የሚሆነው እዚህ በመካከላ
ችሁ ያለውን ጌታ ስለናቃችሁና ፦ ከግብጽ ባል
ወጣን ኖሮ መልካም ነበር በማለት በእርሱ ላይ
ስላጕረመረማችሁ ነው ።'"
21 ሙሴም ለእግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤
"እነሆ እኔ ስድስት መቶ ሺ ሕዝብ በመምራት
ላይ እገኛለሁ ፤ ለአንድ ወር የሚበቃ ሥጋ ልት
ሰጣቸው ቃል ገብተሃል ፤ 22 ታዲያ ምን ያህል
የከብትና የበግ መንጋ ቢታረድ እነርሱን ሊያጠ
ግብ ይችላል? በባሕር ውስጥ ያለው ዓሣ ሁሉ
ቢሰበሰብ ለእነርሱ በቂ ሊሆን ይችላልን?"
23 እግዚአብሔርም "ለኑይሌ ወሰን አለ
ውን? የተናገርሁት ቃል ይፈጸም ወይም አይፈ
ጸም እንደሆን አሁን ሳይዘገይ ታያለህ!" ሲል
መለሰለት ።
24 ስለዚህ ሙሴ ወጥቶ እግዚአብሔር ያለ
ውን ሁሉ ለሕዝቡ ተናገረ ፤ ከሕዝቡ መሪዎች
ሰባውን በአንድነት ሰብስቦ በድንኳኑ ዙሪያ ለተ
ወሰነ ጊዜ ተመድበው እንዲሠሩ አደረገ ።
25 እግዚአብሔርም በደመና ወርዶ ተናገረው ፤
ለሙሴ ከሰጠው መንፈስ ከፊሉን ወስዶ በሰባ
ዎቹ መሪዎች ላይ አሳደረባቸው ፤ መንፈስ በወ
ረደባቸውም ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
እንደ ነቢያት ትንቢት ተናገሩ ፤ ይህን ያደረ
ጉት ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበር ።
26 ከተመዘገቡት ከሰባው መሪዎች መካከል
ሁለቱ ኤልዳድና ሜዳድ የተባሉት ወደ
ድንኳኑ ሳይሄዱ በሰፈር ቆይተው ነበር ፤ እዚ
ያው በሰፈር እንዳሉ መንፈስ ወረደባቸውና እነ
ርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንደ ነቢ
ያት ትንቢት ተናገሩ ። 27 አንድ ወጣት ወደ
ሙሴ ሲሮጥ ሄዶ "ኤልዳድና ሜዳድ በሰፈር
ውስጥ ትንቢት እየተናገሩ ናቸው" ሲል ነገ
ረው ።
28 ከጕልማሳነቱ ጀምሮ የሙሴ ረዳት የነበ
ረው የነዌ ልጅ ኢያሱ "ጌታዬ ሙሴ ሆይ!
ከልክላቸው!" አለው ።
29 ሙሴም "አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን?
እኔስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁሉ ላይ መንፈ
ሱን ቢያወርድና ሁሉም ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው እንደ ነቢያት ትንቢት ቢናገሩ ደስታዬ
ነው!" አለው ። 30 ከዚህ በኋላ ሙሴና ሰባዎቹ
የእስራኤል መሪዎች ወደ ሰፈር ተመለሱ ።

### እግዚአብሔር ድርጭቶችን ላከ

31 በድንገትም እግዚአብሔር ድርጭቶችን
ከባሕር እየነዳ የሚያመጣ ነፋስ ላከ ፤ ድርጭቶ
ችም ከምድር አንድ ሜትር ያህል ከፍ ብለው
እየበረሩ መጡ ፤ በሰፈሩና በሰፈሩ ዙሪያ የተከ
ማቹበት ስፍራ የአንድ ቀን መንገድ ያህል

11፡9 ፦ ዘጸ. 16፡13-15 ።

ንገረው ፤ 38 ጥናዎቹም የተቀደሱት ወደ እግዚ
አብሔር መሠዊያ በቀረቡ ጊዜ ነው ፤ ስለዚህ
በኃጢአታቸው የተገደሉትን የእነዚህን ሰዎች
ጥናዎች ውሰድና በመቀጥቀጥ እንዲሳሱ አድ
ርግ ፤ ስመሠዊያውም መክደኛ እንዲሆኑ አድር
ገህ ሥራቸው ፤ ለእስራኤል ሕዝብ የመቀጣጫ
ማስጠንቀቂያ ይሆናል ።”
39 ስለዚህ አልዓዛር ጥናዎቹን ወስዶ ለመሠ
ዊያው ክዳን ይሆኑ ዘንድ በስሱ ቀጠቀጣቸው ።
40 ይህም የአሮን ዝርያ ያልሆነ ማንኛውም ሰው
ለእግዚአብሔር ዕጣን ያጥን ዘንድ ወደ መሠዊ
ያው መቅረብ እንደማይገባው ለእስራኤላውያን
ሁሉ ማስጠንቀቂያ ይሆናል ፤ ይህ ካልሆነ ግን
እንዲህ የሚያደርግ ሰው ሁሉ እንደ ቆሬሕና
እንደተከታዮቹ ይጠፋል ፤ ይህም ሁሉ የተፈጸ
መው እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለአልዓ
ዛር በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ነበር ።

### አሮን ሕዝቡን አዳነ

41 በማግሥቱ መላው የእስራኤል ማኅበር
“የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑትን ሕዝብ ገድ
ላችኋል” በማለት በሙሴና በአሮን ላይ አጕረ
መረሙ ። 42 ሙሴንና አሮንን ለመቃወም
ሁሉም በአንድነት ከተሰበሰቡ በኋላ ወደ
ድንኳኑ ዞር ብለው ሲመለከቱ የእግዚአብሔርን
መገኘት የሚያመለክተው አንጸባራቂ ብርሃን
ድንኳኑን ሸፍኖት አዩ ፤ 43 ሙሴና አሮንም
መጥተው በድንኳኑ ፊት ለፊት ቆሙ ። 44 እግ
ዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፥ 45 “ከእነ
ዚህ ሕዝብ ርቃችሁ ቁሙ ፤ እኔ እነርሱን በአ
ንድ ጊዜ እደመስሳቸዋለሁ !”
ሁለቱም በግንባራቸው ወደ መሬት ተደፉ ፤
46 ሙሴም አሮንን እንዲህ አለው ፥ “የአንተን
ጥና ወስደህ ከመሠዊያው የእሳት ፍም ጨምር
በት ፤ በፍሙም ላይ ጥቂት ዕጣን አድርግበት ፤
ከዚያም ወደ ሕዝቡ በፍጥነት በመሄድ የማንጻ
ትን ሥርዓት ፈጽምላቸው ፤ ፍጠን ! እነሆ የእ
ግዚአብሔር ቍጣ ከመገለጡ የተነሣ በሕዝቡ
መካከል አባር ቸነፈር መስፋፋት ጀምሮ
አል ።” 47 አሮንም በመታዘዝ ጥናውን ይዞ ወደ
ተሰበሰቡት ሕዝብ መካከል ፈጥኖ ሄደ ፤ አባር
ቸነፈሩ እንደ ጀመረ በተመለከተ ጊዜ ዕጣኑን
በፍሙ ላይ አድርጎ ለሕዝቡ የማንጻትን ሥር
ዓት ፈጸመላቸው ፤ 48 ይህም የአባር ቸነፈሩ
መቅሠፍት እንዲቆም አደረገ ፤ አሮንም በሞቱ
ትና በሕይወት ባሉት መካከል ቆሞ ነበር ።
49 በዚያን ጊዜ የሞቱት ሰዎች ቍጥር ከቆሬሕ
ጋር አምፀው ያለቁትን ሳይጨምር ዐሥራ
አራት ሺ ሰባት መቶ ነበር ፤ 50 ቸነፈሩም
በቆመ ጊዜ አሮን በድንኳኑ ደጃፍ ወደነበረው
ወደ ሙሴ ተመለሰ ።

## ምዕራፍ 17
### የአሮን በትር ልምላሜ

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
2 “የእስራኤል ሕዝብ ከያንዳንዱ የነገድ መሪ
አንዳንድ በትር ተቀብለው ዐሥራ ሁለት በት
ሮች እንዲሰጡህ ጠይቃቸው ፤ የእያንዳንዱንም
ስም በበትሩ ላይ ጻፍ ። 3 በሌዊ ነገድ ስም በቀ
ረበውም በትር ላይ የአሮንን ስም ጻፍበት ፤ ስለ
ያንዳንዱ ነገድ መሪ አንድ በትር ይቅረብ ።
4 እነርሱንም እኔ ወደምመስክበት ድንኳን ወስ
ደህ አንተን በማነጋግርበት ስፍራ በታቦቱ ፊት
ለፊት አኑራቸው ፤ 5 ከዚያም በኋላ እኔ ለክህነት
የምመርጠው ሰው በትሩ በማቈጥቈጥ ትለመል
ማለች ፤ በዚህም ዐይነት እነዚህ የእስራኤል
ሕዝብ በየጊዜው በአንተ ላይ ማጕረምረማቸ
ውን እንዲያቆሙ አደርጋለሁ ።”
6 ስለዚህ ሙሴ ይህንኑ ለእስራኤላውያን ነገ
ራቸው ፤ እያንዳንዱም መሪ በትሩን አምጥቶ
ሰጠው ፤ ስለያንዳንዱ የነገድ መሪ የሚሰጠው
አንዳንድ በትር ሆኖ በአጠቃላይ ዐሥራ ሁለት
በትሮች ቀረቡ ፤ ከእነዚያም በትሮች መካከል
የአሮን በትር ነበረች ፤ 7 ሙሴ በትሮቹን ሁሉ
ወስዶ በድንኳኑ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል
ኪዳን ታቦት ፊት ለፊት አኖራቸው ።
8 በማግሥቱ ሙሴ ወደ ድንኳኑ በገባ ጊዜ
በሌዊ ነገድ ስም የቀረበችው የአሮን በትር ለም
ልማ አገኛት ፤ ይኸውም እንቡጥ አውጥታ በማ
በብ የበሰለ የለውዝ ፍሬ አፍርታ ነበር ፤
9 ሙሴም በትሮቹን ሁሉ አምጥቶ ለእስራኤላው
ያን አሳያቸው ፤ የሆነውን ሁሉ ከተመለከቱ
በኋላ እያንዳንዱ መሪ የራሱን በትር ወሰደ ።
10 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥ “የአ
ሮንን በትር በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት መልሰህ
አኑረው ፤ ዐመፀኞች የሆኑ እስራኤላውያን በእኔ
ላይ ማጕረምረማቸውን ካልተዉ እንደሚሞቱ
ማስጠንቀቂያ ሆኖ ይቀመጥ ።” 11 ሙሴም እግ
ዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ።
12 የእስራኤል ሕዝብ ሙሴን እንዲህ
አሉት ፥ “እንዲህ ከሆነማ እኛ ሁላችንም ማስ
ቃችን ነው ! 13 ወደ ድንኳኑ የሚቀርብ እንኳ
የሚሞት ከሆነ ሁላችንም አሁኑኑ እንደሞትን
ይቈጠራል ።”

## ምዕራፍ 18
### የካህናትና የሌዋውያን ተግባር

1 እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ አለው ፥
“እኔ በምመስክበት ድንኳን ውስጥ በሚከናወ
ነው አገልግሎት ስለሚፈጸመው በደል ሁሉ
አንተና ልጆችህ ፥ ሌዋውያንም ኀላፊነቱን ትሸ
ከማላችሁ ፤ በክህነት አገልግሎት ለሚፈጸመው

---

17፥8-10 ፦ ዕብ. 9፥4 ።

በደል ግን ኀላፊነቱን የምትወስዱት በተለይ
አንተና ልጆችህ ብቻ ናችሁ። 2እንተና ልጆ
ችህ በድንኳኑ ውስጥ በምታገለግሉበት ጊዜ ከእ
ናንተ ጋር በመሥራት ይረዱአችሁ ዘንድ፥
የሌዊ ነገድ የሆኑትን ወገኖችህን ውሰድ፤ 3እነ
ርሱም እናንተን የመርዳት ተግባራቸውን እያከ
ናወኑ ድንኳኑንም የመከባከብ ኀላፊነት ይወስ
ዳሉ፤ ይሁን እንጂ በተቀደሰው ስፍራና በመሠ
ዊያው ላይ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት መንካት
አይኖርባቸውም፤ ነክተው ቢገኙ ግን እነርሱም
እናንተም በአንድነት ትሞታላችሁ። 4እነርሱ
ዘወትር ከእናንተ ጋር መሥራትና በድንኳኑ
ውስጥ ስለተሰጣቸው አገልግሎት ሁሉ ኀላፊነ
ታቸውን መፈጸም አለባቸው፤ ነገር ግን ሌዋዊ
ያልሆነ ማንኛውም ሰው ከእናንተ ጋር አብሮአ
ችሁ እንዲሠራ አይፈቀድለትም። 5ቍጣዬ በእ
ስራኤል ሕዝብ ላይ እንደገና እንዳይገለጥ በተቀ
ደሰው ስፍራና በመሠዊያው ላይ ያለውን የአገ
ልግሎት ኀላፊነት የምትፈጽሙት እናንተና
ልጆቻችሁ ብቻ ናችሁ። 6ዘመዶቻችሁን ሌዋ
ውያንን ከእስራኤላውያን መካከል የመረጥሁና
ለእናንተም ስጦታ አድርጌ የመደብሁ እኔ ነኝ፤
እነርሱ በድንኳኑ ውስጥ የተመደቡበትን ተግ
ባር ያከናውኑ ዘንድ ለእኔ የተለዩ ናቸው።
7ነገር ግን መሠዊያውንና ከመጋረጃው በስተው
ስጥ በኩል ያለውን ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚመለ
ከተውን የክህነት ኀላፊነት የምትፈጽሙ አን
ተና ልጆችህ ብቻ ናችሁ፤ የክህነትን አገልግ
ሎት ዕድል ፈንታ አድርጌ ስለሰጠኋችሁ ይህ
ሁሉ ኀላፊነት የእናንተ ነው፤ ሌዋዊ ያልሆነ
ማንኛውም ሰው ወደ ንዋያተ ቅድሳት ቢቀርብ
ይሞታል።”

### የካህናቱ ድርሻ

8ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ
አለው፥ “ለእኔ የሚቀርበውን የማይቃጠለውን
ልዩ መባ ሁሉ ለአንተ የሰጠሁህ መሆኑን አስታ
ውስ፤ እርሱ ለዘላለም ለአንተና ለዝርያዎችህ
ሁሉ ድርሻ እንዲሆን ሰጥቻችኋለሁ፤ 9ለእኔ
ከሚቀርበው እጅግ ከተቀደሰ መባ ሁሉ፥ ከእ
ህል ቊርባን፥ ስለ ኃጢአት ስርየትና ስለ በደል
ካሣ ከሚቀርበውም መባ ሁሉ፥ በእሳት የማይ
ቃጠለው የመባ ድርሻ የአንተና የልጆችህ
ነው። 10በተቀደሰው ስፍራ ሆናችሁ እነዚህን
ሁሉ ትበላላችሁ፤ የተቀደሱ መሆናቸውን በመ
ገንዘብ ወንዶች ብቻ ይመገቡአቸው።
11“በተጨማሪም እስራኤላውያን በእኔ ፊት
ወደ ላይና ወደ ታች በመወዝወዝ የሚያቀርቡ
ዋቸው ልዩ ስጦታዎች ሁሉ የእናንተ ይሆ
ናሉ፤ እነርሱን ለአንተ፥ ለወንዶችና ለሴቶች
ልጆችህ ለሚመጡት ዘመናት ሁሉ ሰጥቻለሁ፤
በሕግ መሠረት በሥርዓት ንጹሕ የሆነ ማንኛ
ውም የቤተሰብህ አባል ሊመገባቸው ይችላል።
12“እስራኤላውያን የሚሰጡኝን ምርጥ
የሆነ በኵራት፥ ይኸውም የወይራ ዘይት፥ የወ
ይን ጠጅና እህል ለእናንተ እሰጣችኋለሁ።
13ሁሉም በኵራት የእናንተ ዕድል ፈንታ ስለ
ሚሆን በሕጉ መሠረት በሥርዓት ንጹሕ የሆነ
የቤተሰባችሁ አባል ሁሉ ሊመገበው ይችላል።
14“በእስራኤል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለእኔ
የተለየ ነገር ሁሉ ለእናንተ ይሆናል።
15“እስራኤላውያን ለእኔ የሚያቀርቡት የሰ
ውም ሆነ የእንስሳ በኵር ሁሉ የእናንተ ይሆ
ናል፤ ነገር ግን የሰውን የበኵር ልጅ ለመዋጀት
ዋጋውን በጥሬ ገንዘብ መቀበል አለባችሁ፤ እን
ዲሁም በሥርዓት ንጹሕ ስላልሆነው የእንስሳ
በኵር ምትክ ዋጋውን በጥሬ ገንዘብ መቀበል
ትችላላችሁ፤ 16አንድ ወር የሞላቸው ሕፃናት
በይፋ በተመደበው ዋጋ መሠረት አምስት ጥሬ
ብር የቤዛ ዋጋ ተከፍሎላቸው ሊዋጁ ይችላሉ።
17የላም፥ የበግና የፍየል በኵር ግን የሚዋጁ
በት ዋጋ አይከፈልባቸውም፤ እነርሱ በፍጹም
የእኔ ስለሆኑ መሥዋዕት ሆነው መቅረብ ይኖር
ባቸዋል፤ ደማቸውን በመሠዊያው ላይ አፍስ
ሱት፤ ስባቸውንም መዓዛው እኔን ደስ የሚያ
ሰኝ መሥዋዕት እንዲሆን በእሳት አቃጥሉት።
18ከእነርሱ የሚገኘውም ሥጋ ወደ ላይና ወደ
ታች በመወዝወዝ ልዩ መባ ሆኖ እንደሚቀር
በው እንደ ፍርምባውና እንደ ቀኙ ወርች ለእና
ንተ ይሰጣል።
19“እስራኤላውያን ለእኔ የሚያቀርቡአቸ
ውን ልዩ ስጦታዎች ሁሉ ለእናንተ፥ ለወንዶ
ችና ለሴቶች ልጆቻችሁ ለሚመጡት ዘመናት
ሁሉ ሰጥቻችኋለሁ፤ ይህም ከእናንተና ከዝርያ
ዎቻችሁ ሁሉ ጋር የምገባው የማይሻር የጨው
ቃል ኪዳን ነው።”
20እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ አለው፥
“ለትውልድ የሚተላለፍ ምንም ዐይነት ርስት
አትቀበልም፤ ከእስራኤልም ምድር የትኛውም
ክፍል ለአንተ አይሆንም፤ እኔ እግዚአብሔር
ራሴ ለአንተ ርስትህ ነኝ።”

### የሌዋውያን ድርሻ

21እግዚአብሔር እንዲህ አለ፥ “የእስራኤል
ሕዝብ ለእኔ የሚያመጡትን ዐሥራት ሁሉ የሌ
ዋውያን ድርሻ እንዲሆን ሰጥቻቸዋለሁ፤ ይህም
እኔ በምመለከበት ድንኳን ውስጥ ለሚሰጡት
አገልግሎት ደመወዝ ይሆንላቸዋል። 22ሌሎች
እስራኤላውያን ግን በራሳቸው ላይ የሞት
ቅጣት እንዳያስከትሉ ዳግመኛ ወደ ድንኳኑ
መቅረብ የለባቸውም፤ 23ከእንግዲህ ወዲህ
ለድንኳኑ ከብካቤ የሚያደርጉትና ለእርሱም

18፡14 ፦ ዘሌ. 27፡28። 18፡21 ፦ ዘሌ. 27፡30-33፤ ዘዳ. 14፡22-29።

ለሞአብ ጣዖት የተሠዋውን መሥዋዕት እንዲመ
ገቡ ጋበዙአቸው ፤ እስራኤላውያንም የመሥዋዕ
ቱን ምግብ በልተው "የፔዖር ባዓል" ለተባለ
ውም ጣዖት ሰገዱ ፤ 3 ስለዚህም እግዚአብሔር
በእነርሱ ላይ ተቈጥቶ ፥ 4 ሙሴን እንዲህ
አለው ፤ "የእስራኤልን መሪዎች ሁሉ ወስደህ
ለእኔ በመታዘዝ በጠራ ፀሐይ በሕዝብ ፊት እን
ዲገደሉ አድርግ ፤ በዚህም ሕዝብ ላይ የነደ
ደው ቊጣዬ ከዚያ በኋላ ይበርዳል ።" 5 ሙሴም
ባለሥልጣኖችን "እያንዳንዳችሁ በየነገዳችሁ
መካከል ለፔዖር ባዓል የሰገደውን ሁሉ ግደሉ"
አላቸው ።

6 ሙሴና መላው ማኅበር እግዚአብሔር በሚ
መለክበት ድንኳን ደጃፍ ተገኝተው በመጨነቅ
በሚያለቅሱበት ጊዜ ፥ ከእስራኤላውያን አንዱ
አንዲት ምድያማዊት ሴት ይዞ በእነርሱ ፊት
በማለፍ ወደ ቤተሰቡ አቀረባት ። 7 የካህኑ የአ
ሮን የልጅ ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ይህን
ባየ ጊዜ ፥ ከተቀመጠበት በመነሣት ከጉባኤው
መካከል ወጥቶ ሄደ ፤ ጦርም አንሥቶ ፥ 8 ሰውየ
ውና ሴቲቱ ወዳሉበት ድንኳን ገባ ፤ ሁለቱንም
በአንድነት በጦር ወግቶ ገደላቸው ፤ በዚህም
ሀይነት እስራኤላውያንን በማጥፋት ላይ የነበ
ረው መቅሠፍት ቆመ ፤ 9 ነገር ግን እስከዚያው
ሰዓት ድረስ ያ መቅሠፍት ሃያ አራት ሺ ሕዝብ
አጥፍቶ ነበር ።

10 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፥
11 "ፊንሐስ ባደረገው ነገር ምክንያት በእስራ
ኤል ሕዝብ ላይ ያለኝ ቊጣ በርዶአል ፤ ፊን
ሐስ ከእኔ በቀር ለሌላ አምላክ የሚሰግዱትን
መታገሥ አልፈለገም ፤ በቊጣዬ እስራኤልን
ያላጠፋሁትም እርሱ ስለእኔ ባሳየው ቅንአት
ነው ። 12 ስለዚህ እኔ ከእርሱ ጋር ለዘላለም
ጸንቶ የሚኖር ቃል ኪዳን የምገባ መሆኔን ንገ
ረው ። 13 እርሱ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ እንዲ
ኖር ስላልፈቀደና የሕዝቡንም ኃጢአት ይቅር
ስላሳለ ፥ እርሱና ዘሮቹ በሙሉ ለዘላለም ካህናት
ይሆናሉ ።"

14 ከምድያማዊቱ ሴት ጋር የተገደለው እስራ
ኤላዊ ስም የሳሉ ልጅ ዚምሪ ሲሆን ፥ እርሱም
በስምዖን ነገድ የጐሳ አለቃ ነበር ። 15 የሴቲ
ቱም ስም ኮዝቢ ይባል ነበር ፤ "ጹር" ተብሎ
የሚጠራው አባትዋም በአንድነት የሚኖሩ የጥ
ቂት ምድያማውያን ጐሳዎች አለቃ ነበር ።

16 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ አዘ
ዘው ፥ 17 "በምድያማውያን ላይ አደጋ ጥላችሁ
ደምስሱአቸው ፤ 18 ይህንንም የምታደርጉት እና
ንተን በፔዖር በማታለል ግፍ ስለሠሩባችሁና
በፔዖር በወረደው መቅሠፍት ምክንያት በተገደ
ለችው በአለቃቸው ልጅ በኮዝቢ አማካይነት
በፈጸሙት ሸንገላ ነው ።"

## ምዕራፍ 26
### ሁለተኛው የሕዝብ ቈጠራ

1 መቅሠፍቱ ከቆመ በኋላ እግዚአብሔር
ሙሴንና የአሮንን ልጅ አልዓዛርን እንዲህ አላ
ቸው ፥ 2 "በመላው የእስራኤል ማኅበር በየቤተ
ሰቡ ዕድሜአቸው ሃያ ዓመት የሞላቸውንና ከዚ
ያም በላይ የሆኑትን ፥ ወታደር ሆነው ለማገል
ገል ብቃት ያላቸውን ወንዶች ልጆች ሁሉ
ቊጠሩ ።" 3-4 ሙሴና አልዓዛር ትእዛዙን ተቀ
ብለው በሃያ ዓመት ዕድሜ ክልልና ከዚያም
በላይ የሆኑትን ወንዶች ሁሉ በአንድነት እንዲ
ሰበሰቡ አደረጉ ፤ እነርሱም የተሰበሰቡት በኢያ
ሪኮ ትይዩ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በሚገኘው
በሞአብ ሜዳ ላይ ነበር ።

ከግብጽ ምድር የወጡትም እስራኤላውያን
እነዚህ ነበሩ ፥

5 የያዕቆብ የበኵር ልጅ የሆነው የሮቤል
ነገድ የጐሳ መሪዎች ሐኖክ ፥ ፋሉ ፥ 6 ሔጽሮ
ንና ካርሚ የተባሉት ናቸው ፤ 7 ከእነዚህም
ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር አርባ
ሦስት ሺ ሰባት መቶ ሠላሳ ነበር ፤ 8 የፋሉ ዘሮ
ችም ኤሊአብና 9 የኤሊአብ ልጆች ነሙኤል ፥
ዳታንና አቤሮም ነበሩ ፤ ዳታንና አቤሮምም
በማኅበሩ ተመርጠው የነበሩት ሲሆኑ ፥ እነር
ሱም ከቆራሕና ከተከታዮቹ ጋር ተባብረው በእ
ግዚአብሔር ላይ ባመፁ ጊዜ ሙሴንና አሮንን
የተፈታተኑአቸው ናቸው ። 10 እነርሱንም
ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው ፤ እሳትም ወርዳ
ሁለት መቶ ኀምሳውን ሰዎች በበላች ጊዜ ከቆ
ራሕና ከተከታዮቹ ጋር ሞቱ ፤ ለሕዝቡም ማስ
ጠንቀቂያ ሆኑ ። 11 የቆራሕ ልጆች ግን አልሞ
ቱም ነበር ።

12 የስምዖን ነገድ የጐሳ መሪዎች ነሙኤል ፥
ያሚን ፥ ያኪን ፥ 13 ዜራሕና ሻኡል የተባሉት
ናቸው ። 14 ከእነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ
ጠቅላላ ቊጥር ሃያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ
ነበር ።

15 የጋድ ነገድ የጐሳ መሪዎች ጼፎን ፥
ሐጊ ፥ ሹኒ ፥ 16 ኦዝኒ ፥ ዔሪ ፥ 17 አሮድና አር
ኤሊ የተባሉት ናቸው ፤ 18 ከእነዚህም ጐሳዎች
የወንዶቹ ብቻ ቊጥር አርባ ሺ አምስት መቶ
ነበር ።

19-21 የይሁዳ ነገድ የጐሳ መሪዎች ሺላ ፥
ፋሬስ ፥ ዛራሕና የፋሬስ ልጆች ሔጽሮንና
ሐሙል የተባሉት ናቸው ፤ (ከይሁዳ ልጆች
ሁለቱ ዔርና ኦናን በከነዓን ምድር ሞቱ ።)
22 ከእነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ቊጥር
ሰባ ስድስት ሺ አምስት መቶ ነበር ።

23 የይሳኮር ነገድ የጐሳ አለቆች ቶላዕ ፥
ፉዋ ፥ 24 ያሹብና ሺምሮን የተባሉት ናቸው ፤

26፥1-5 ፡- ዘኍ. 1፥1-46 ።

25 ከእነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ቊጥር
ስልሳ አራት ሺ ሦስት መቶ ነበር።
26 የዛብሎን ነገድ የጐሳ መሪዎች ሴሬድ፥
ኤሎንና ያሕለኤል የተባሉት ናቸው፤ 27 ከእነ
ዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር
ስልሳ ሺ አምስት መቶ ነበር።
28 የምናሴና የኤፍሬም አባት የሆነው የዮ
ሴፍ ነገዶች።
29 የምናሴ ነገድ፤ የምናሴ ልጅ ማኪር ገለዓ
ድን ወለደ፤ የሚከተሉትም የጐሳ መሪዎች የገ
ለዓድ ዘሮች ናቸው፤ 30 እነርሱም ኢዔዜር፥
ሔሌቅ፥ 31 አሥሪኤል፥ ሼኬም፥ 32 ሸሚዳዕና
ሔፌር የተባሉት ናቸው፤ 33 የሔፌር ልጅ
ጸሎፍሐድ ከሴቶች በቀር ወንዶች ልጆች አልነ
በሩትም፤ እነርሱም ማሕላ፥ ኖዓ፥ ሖግላ፥
ሚልካና ቲርጻ ተብለው የሚጠሩ ነበሩ፤ 34 ከእ
ነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር
ኀምሳ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ነበር።
35 የኤፍሬም ነገድ የጐሳ መሪዎች ሹቴ
ላሕ፥ ቤኬርና ታሐን የተባሉት ናቸው፤
36 የሹቴላሕ ዘሮች የዔራን ጐሳዎች ናቸው፤
37 ከእነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ
ቊጥር ሠላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ ነበረ።
እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የዮሴፍ ዝርያዎች
ነበሩ።
38 የብንያም ነገድ የጐሳ መሪዎች ቤላዕ፥
አሽቤል፥ አሒራም፥ 39 ሸፉፋምና ሑፋም
ናቸው፤ 40 የቤላዕም ዘሮች የአረድና የናዕማን
ጐሳዎች ናቸው፤ 41 ከእነዚህም ጐሳዎች የወን
ዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር አርባ አምስት ሺ ስድ
ስት መቶ ነበር።
42 የዳን ነገድ የጐሳ መሪ ሹሐም ሲሆን፥
43 ከእነርሱም የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር
ስልሳ አራት ሺ አራት መቶ ነበር።
44 የአሴር ነገድ የጐሳ መሪዎች ይምና፥
ይሽዊና በሪዓ ናቸው፤
45 የበሪዓም ዘሮች የሔቤርና የማልኪኤል
ጐሳዎች ናቸው። 46 አሴርም ሤራሕ የምትባል
ሴት ልጅ ነበረችው፤ 47 ከእነዚህም ጐሳዎች
የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ድምር ኀምሳ ሦስት ሺ
አራት መቶ ነበር።
48 የንፍታሌም ነገድ የጐሳ መሪዎች ያሕጽ
ኤል፥ ጉኒ፥ 49 ዬጼርና ሺሌም ናቸው፤ 50 ከእ
ነዚህም ጐሳዎች የወንዶቹ ብቻ ጠቅላላ ቊጥር
አርባ አምስት ሺ አራት መቶ ነበር። 51 በዚ
ህም ሁኔታ የእስራኤላውያን ወንዶች ጠቅላላ
ቊጥር ስድስት መቶ አንድ ሺ ሰባት መቶ
ሠላሳ ነበር።
52 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፥
53 "የቊጥራቸውን ብዛት እያየህ ምድሪቱን በነ
ገዶች መካከል አከፋፍል፤ 54-56 ምድሪቱንም
ስታከፋፍል እንደየአባታቸው ስም ዕጣ በማው
ጣት ሲሆን ትልቁን ድርሻ ለትልቅ ነገድ፥ ትን
ሹንም ድርሻ ለትንሽ ነገድ ስጥ።"
57 የሌዊ ነገድ የጌርሾንን፥ የቀሃትንና የመራ
ሪን ጐሳዎች የሚያጠቃልል ነበር። 58 የእነር
ሱም ዘሮች የሊብኒ፥ የኬብሮን፥ የማሕሊ፥
የሙሺና የቆሬሕ ጐሳዎች ናቸው፤ የቀሃት
ልጅ ዓምራም ሲሆን፥ 59 እርሱም በግብጽ የተ
ወለደችውን የሌዊን ሴት ልጅ ዮኬቤድን አግ
ብቶ ነበር፤ እርስዋም አሮንና ሙሴ የተባሉትን
ሁለት ወንዶች ልጆችንና ሚርያም የተባለች
ውን አንዲት ሴት ልጅ ወለደችለት። 60 አሮ
ንም ናዳብ፥ አቢሁ፥ አልዓዛርና ኢታማር የተ
ባሉ አራት ወንዶች ልጆች ነበሩት። 61 ናዳብና
አቢሁ ያልተቀደሰ እሳት ለእግዚአብሔር ከማቅ
ረባቸው የተነሣ ተቀሥፈው ሞቱ። 62 ዕድሜአ
ቸው አንድ ወርና ከዚያም በላይ የሆነ የወን
ዶች ሌዋውያን ጠቅላላ ቊጥር ሃያ ሦስት ሺ
ሆነ፤ እነርሱም ከሌሎቹ እስራኤላውያን ተለይ
ተው ተመዘገቡ፤ ይህም የሆነበት ምክንያት
በእስራኤል ምድር ምንም ዐይነት የርስት
ድርሻ ስላልተሰጣቸው ነበር።
63 ሙሴና አልዓዛር በኢያሪኮ ትይዩ ከዮርዳ
ኖስ ወንዝ ማዶ ባለው በሞአብ ሜዳ እስራኤላ
ውያንን በቈጠሩበት ጊዜ የመዘገቡአቸው የጐሳ
መሪዎች እነዚህ ነበሩ። 64 በሲና በረሐ በመጀ
መሪያው የሕዝብ ቈጠራ ጊዜ ሙሴና አሮን
ከመዘገቡአቸው ወንዶች አንድም ተርፎ የቀረ
አልነበረም። 65 ምክንያቱም "ሁሉም በምድረ
በዳ ይሞታሉ" ብሎ እግዚአብሔር ተናግሮ ስለ
ነበር ነው፤ ስለዚህም ከይፉኔ ልጅ ከካሌብና
ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር ሁሉም ሞተዋል።

## ምዕራፍ 27
### የጸሎፍሐድ ሴቶች ልጆች ጥያቄ

1 የሔፌር፥ የገለዓድ፥ የማኪር፥ የምናሴ፥
የዮሴፍ ልጅ የሆነው ጸሎፍሐድ፥ ማሕላ፥
ኖዓ፥ ሖግላ፥ ሚልካና ቲርጻ ተብለው የሚጠሩ
ሴቶች ልጆች ነበሩት። 2 እነርሱም እግዚአብ
ሔር በሚመለከበት ድንኳን ደጃፍ ሄደው
መላው ማኅበርና የሕዝቡ መሪዎች ባሉበት
በሙሴና በአልዓዛር ፊት ቆመው እንዲህ አሉ፥
3 "አባታችን አንድ እንኳ ወንድ ልጅ ሳይወ
ልድ በምድረ በዳ ሞተ፤ እርሱ በእግዚአብሔር
ላይ ካመፁት ከቆሬሕ ተከታዮች ጋር ተባባሪ
አልነበረም፤ የሞተውም በራሱ ኃጢአት ምክን
ያት ነው፤ 4 ታዲያ ወንድ ልጅ ባለመውለዱ
ብቻ የአባታችን ስም ከእስራኤል ተፍቆ መጥ
ፋት ይገባዋልን? ስለዚህ በአባታችን ዘመዶች

---

26፥52-56 ፦ ዘኍ. 34፥13፤ ኢያሱ 14፥1-2። 26፥60 ፦ ዘኍ. 3፥2። 26፥61 ፦ ዘሌ. 10፥1-2፤ ዘኍ. 3፥4።
26፥65 ፦ ዘኍ. 14፥26-35።

የመንጻትን ሥርዓት ትፈጽማላችሁ ። 6 ይህንንም
ሁሉ መሥዋዕት በየወሩ መጀመሪያ ቀን ከሚቀ
ርበው የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል ቍር
ባን ፥ እንዲሁም በየቀኑ ከሚቀርበው የሚቃ
ጠል መሥዋዕት የእህል ቍርባንና የወይን ጠጅ
መባ ጋር ተጨማሪ በማድረግ ታቀርባላችሁ ፤
ይህም መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
የምግብ ቍርባን ይሆናል ።

### ኃጢአት በሚሰረይበት ቀን የሚቀርብ መሥዋዕት
(ዘሌ. 23፥26-32)

7 ሰባተኛው ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን ለአ
ምልኮ ትሰበሰባላችሁ ፤ በዚያን ቀን ምግብ አት
መገቡም ፤ ሥራም አትሠሩም ፤ 8 ምንም ነውር
የሌለበትን አንድ ወይፈን ፥ አንድ አውራ በግ ፥
አንድ ዓመት የሞላቸው ሰባት ተባዕት የበግ
ጥቦቶች መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ ።
9 ተገቢ የሆነውንም የእህል ቍርባን በወይራ
ዘይት የተለወሰ ዱቄት አቅርቡ ፤ ይኸውም ከወ
ይፈኑ ጋር ሦስት ኪሎ ዱቄት ፥ ከአውራው በግ
ጋር ሁለት ኪሎ ዱቄት ፥ 10 ከእያንዳንዱም
የበግ ጥቦት ጋር አንድ ኪሎ ዱቄት ታቀርባላ
ችሁ ። 11 ስለ ኃጢአት ስርየትም የሚሆን አንድ
ተባዕት ፍየል ታቀርባላችሁ ፤ እርሱም ለሕዝቡ
የመንጻት ሥርዓት በተፈጸመበት ጊዜ ከሚቀር
በው ተባዕት ፍየል እንዲሁም ከእህል ቍርባንና
ከወይን ጠጅ መባ ፥ በየቀኑ ከሚቀርበው የሚቃ
ጠል መሥዋዕት ጋር ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ
ነው ።

### በዳስ በዓል ጊዜ የሚቀርብ መሥዋዕት
(ዘሌ. 23፥33-44)

12 ሰባተኛው ወር በገባ በዐሥራ አምስተ
ኛው ቀን በአንድነት ለአምልኮ ትሰበሰባላችሁ ፤
ይህንንም በዓል ለእግዚአብሔር ክብር በመስ
ጠት ሰባት ቀን አክብሩ ፤ በዚህም ቀን ምንም
ሥራ አትሥሩ ። 13 በዚሁ በመጀመሪያው ቀን
ምንም ነውር የሌለባቸውን ዐሥራ ሦስት ወይፈ
ኖች ፥ ሁለት የበግ አውራዎች ፥ አንድ ዓመት
የሞላቸው ዐሥራ አራት ተባዕት የበግ ጥቦቶች
መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የምግብ
ቍርባን አድርጋችሁ አቅርቡ ። 14 ተገቢ ስለሆነ
ውም የእህል ቍርባን በወይራ ዘይት የተለወሰ
ዱቄት አቅርቡ ፤ ይኸውም ከእያንዳንዱ ወይፈን
ጋር ሦስት ኪሎ ዱቄት ፥ ከእያንዳንዱ አውራ
በግ ጋር ሁለት ኪሎ ዱቄት ፥ 15 ከእያንዳንዱም
ጥቦት ጋር አንድ ኪሎ ዱቄት ታቀርባላችሁ ፤
16 ስለ ኃጢአት ስርየትም የሚሆን አንድ ተባ
ዕት ፍየል ታቀርባላችሁ ፤ ይህንንም ሁሉ መሥ
ዋዕት የምታቀርቡት በየቀኑ ከሚቀርበው የሚ
ቃጠል መሥዋዕት የእህል ቍርባንና የወይን
ጠጅ መባ ጋር ተጨማሪ በማድረግ ነው ።
17 በሁለተኛው ቀን ምንም ነውር የሌለባቸ
ውን ዐሥራ ሁለት ወይፈኖች ፥ ሁለት አውራ
በጎች ፥ አንድ ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት
ተባዕት የበግ ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ፤ 18-19 እነ
ዚህንም በመጀመሪያ ቀን ከቀረበው መሥዋዕት
ሁሉ ጋር አብራችሁ ታቀርባላችሁ ።
20 በሦስተኛው ቀን ምንም ነውር የሌለባቸ
ውን ዐሥራ አንድ ወይፈኖች ፥ ሁለት አውራ
በጎች ፥ አንድ ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት
የበግ ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ፤ 21-22 እነዚህንም
በመጀመሪያው ቀን ከቀረበው መሥዋዕት ሁሉ
ጋር አብራችሁ ታቀርባላችሁ ።
23 በአራተኛው ቀን ነውር የሌለባቸው
ዐሥር ወይፈኖች ፥ ሁለት አውራ በጎች ፥ አንድ
ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት ተባዕት የበግ
ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ፤ 24-25 እነዚህንም በመጀ
መሪያው ቀን ከቀረበው መሥዋዕት ጋር አብራ
ችሁ ታቀርባላችሁ ።
26 በአምስተኛው ቀን ነውር የሌለባቸውን
ዘጠኝ ወይፈኖች ፥ ሁለት አውራ በጎች ፥ አንድ
ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት ተባዕት የበግ
ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ፤ 27-28 እነዚህንም በመጀ
መሪያው ቀን ከቀረበው መሥዋዕት ጋር አብራ
ችሁ ታቀርባላችሁ ።
29 በስድስተኛው ቀን ነውር የሌለባቸውን
ስምንት ወይፈኖች ፥ ሁለት አውራ በጎች ፥
አንድ ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት ተባዕት
የበግ ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ። 30-31 እነዚህንም
በመጀመሪያው ቀን ከቀረበው መሥዋዕት ሁሉ
ጋር አብራችሁ ታቀርባላችሁ ።
32 በሰባተኛውም ቀን ነውር የሌለባቸውን
ሰባት ወይፈኖች ፥ ሁለት የአውራ በጎች ፥
አንድ ዓመት የሞላቸው ዐሥራ አራት ተባዕት
የበግ ጥቦቶች ታቀርባላችሁ ። 33-34 እነዚህንም
በመጀመሪያው ቀን ከቀረበው መሥዋዕት ጋር
አብራችሁ ታቀርባላችሁ ።
35 በስምንተኛው ቀን በአንድነት ለአምልኮ
ትሰበሰባላችሁ ፤ በዚያም ቀን ምንም ሥራ አት
ሠሩም ፤ 36 ምንም ነውር የሌለባቸውን አንድ
ወይፈን ፥ አንድ አውራ በግ ፥ አንድ ዓመት
የሞላቸው ሰባት ተባዕት የበግ ጥቦቶች ፥ መዓ
ዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የምግብ
ቍርባን አድርጋችሁ የሚቃጠል መሥዋዕት
ታቀርባላችሁ ። 37-38 ከእነዚህም ጋር ለመጀመ
ሪያው ቀን የተመደበውን መሥዋዕት ሁሉ አብ
ራችሁ አቅርቡ ።

29፥7-11 ፦ ዘሌ. 16፥29-34 ።

[39]በታወቁት በዓላት ላይ ለእግዚአብሔር
ስለምታቀርቡት የሚቃጠል መሥዋዕት ፥ የእ
ህል ቊርባን ፥ የወይን ጠጅ መባና ስለ ደኅን
ነት የሚቀርበው የኅብረት መሥዋዕት የተሰ
ጡት የሥርዓት መመሪያዎች እነዚህ ናቸው ፤
ይህንንም ሁሉ መሥዋዕት የምታቀርቡት ስለ
ስእለት መፈጸም ወይም በበጎ ፈቃድ ከሚቀር
በው መሥዋዕት ሁሉ ጋር ተጨማሪ አድርጋ
ችሁ ነው ።
[40]በዚህ ዐይነት ሙሴ እግዚአብሔር ያዘዘ
ውን ሁሉ ለእስራኤል ሕዝብ ነገራቸው ።

## ምዕራፍ 30

### ስለ ስእለት የተሰጠ የሥርዓት መመሪያ

[1]ሙሴ ለእስራኤል ነገዶች መሪዎች እግዚአ
ብሔር ያዘዛቸውን የሚከተሉትን የሥርዓት
መመሪያዎች ሰጠ ፤ [2]አንድ ሰው ለእግዚአብ
ሔር አንድ ነገር ለመስጠት ቢሳል ወይም ከአ
ንድ ነገር ለመከልከል በመሐላ ቃል ቢገባ ፥
አደርጋለሁ ያለውን ሁሉ መፈጸም አለበት
እንጂ የሰጠውን የተስፋ ቃል ማስቀረት አይገባ
ውም ።
[3]ገና በአባትዋ ቤት የምትኖር ልጃገረድ ለእ
ግዚአብሔር አንድ ነገር ለመስጠት ብትሳል
ወይም ከአንድ ነገር ለመከልከል በመሐላ ቃል
ብትገባ ፥ [4]አባትዋ ስለዚህ ጉዳይ ሰምቶ ካልተ
ቃወማት በቀር ስእለትዋን ወይም የገባችውን
የመሐላ ቃል መፈጸም አለባት ። [5]አባትዋ ስለ
ጉዳዩ ሰምቶ ስእለትዋን እንዳትፈጽም የሚቃወ
ማት ከሆነ ግን ስእለትዋን የመፈጸም ግዴታ
አይኖርባትም ፤ ስእለትዋን ለመፈጸም ያልቻለ
ችው አባትዋ ስለከለከላት በመሆኑ ምክንያት
እግዚአብሔር ይቅርታ ያደርግላታል ።
[6]ባል ያላገባች ሴት አስባም ሆነ በግድየለሽ
ነት ስእለት ካደረገች ወይም ከአንድ ነገር ለመ
ከልከል በመሐላ ቃል ከገባች በኋላ ባል ብታ
ገባ ፥ [7]ባልዋ ስለ ጉዳዩ ሰምቶ ካልከለከላት
በቀር ስእለትዋንም ሆነ በመሐላ የገባችውን
ቃል መፈጸም አለባት ። [8]ባልዋ ስለ ጉዳዩ
ሰምቶ ከከለከላት ግን የመፈጸም ግዴታ የለባ
ትም ፤ ስእለትዋን ለመፈጸም ያልቻለችው
ባልዋ ስለከለከላት በመሆኑ ምክንያት እግዚአብ
ሔር ይቅርታ ያደርግላታል ።
[9]ባልዋ የሞተባት መበለት ወይም ከባልዋ
የተፋታች ሴት ማንኛቸውንም ስእለት ሆነ
ወይም ከአንድ ነገር ለመከላከል በመሐላ የገባች
ውን ቃል መፈጸም አለባት ።
[10]ባል ያገባች ሴት ስእለት ብትሳል ወይም
ከአንድ ነገር ለመከላከል በመሐላ ቃል ብት
ገባ ፥ [11]ባልዋ ስለ ጉዳዩ ሰምቶ ካልተቃወማት
በቀር ስእለትዋንም ሆነ ከአንድ ነገር ለመከላ
ከል የገባችውን መሐላ መፈጸም ይኖርባታል ፤
[12]ባልዋ ስለ ጉዳዩ ሰምቶ ስእለትዋን እንዳትፈ
ጽም ቢከለክላት ግን የመፈጸም ግዴታ የለባ
ትም ፤ ስእለትዋን ለመፈጸም ያልቻለችው
ባልዋ ስለከለከላት በመሆኑ ምክንያት እግዚአብ
ሔር ይቅርታ ያደርግላታል ። [13]ባልዋ ማንኛው
ንም ስእለት ሆነ መሐላ የመፍቀድ ወይም የመ
ቃወም መብት አለው ። [14]ነገር ግን ባልዋ ስለ
ጉዳዩ በሰማበት ቀን ማግሥት ምንም ተቃውሞ
ያላቀረበ ከሆነ ስእለትዋንና በመሐላ የገባችውን
ቃል ሁሉ መፈጸም ይኖርባታል ፤ ምክንያቱም
ስለ ጉዳዩ በሰማበት ቀን ተቃውሞ አለማቅረቡ
ፈቃደኛ መሆኑን ያረጋግጣል ። [15]ነገር ግን
ቆየት ብሎ ስእለቱን የሚቃወም ከሆነ ስለእስቱ
አለመፈጸም ኀላፊ ይሆናል ።
[16]ሳታገባ በአባትዋ ቤት የምትኖር ልጃገረድ
ወይም ያገባች ሴት ስእለት ወይም የመሐላ
ቃል በምትገባበት ጊዜ ስለምትከተለው ደንብ
ሁሉ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የሥርዓት
መመሪያ ይህ ነው ።

## ምዕራፍ 31

### በምድያማውያን ላይ የተደረገ ጦርነት

[1]እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
[2]“በእስራኤል ሕዝብ ላይ ስለፈጸሙት በደል
ምድያማውያንን ቅጣ ፤ ይህንንም ካደረግህ
በኋላ አንተ ትሞታለህ ።”
[3]ስለዚህ ሙሴ ሕዝቡን እንዲህ አለ ፥
“ምድያማውያን በእግዚአብሔር ላይ ስለፈጸ
ሙት በደል በእነርሱ ላይ አደጋ ጥላችሁ ትቀ
ጡአቸው ዘንድ ለጦርነት ተዘጋጁ ፤ [4]ከእያንዳ
ንዱ የእስራኤል ነገድ አንዳንድ ሺ ወንዶችን
መርጣችሁ ወደ ጦርነቱ ላኩ ።”
[5]ስለዚህ ከእያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሺ
ተመርጦ ዐሥራ ሁለት ሺ ሰዎች ለጦርነት ተዘ
ጋጁ ። [6]እነርሱንም ሙሴ በካህኑ በአልዓዛር
ልጅ በፊንሐስ መሪነት ወደ ጦርነት ላካቸው ፤
ፊንሐስ በንዋያተ ቅድሳቱና ምልክት ለመስጠት
በሚነፉት መለከቶች ላይ ኀላፊነት የነበረው
ነው ። [7]እነርሱም እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው
መሠረት በምድያማውያን ላይ አደጋ ጥለው
ወንዶቹን በሙሉ ገደሉ ። [8]አምስቱንም የምድ
ያም ነገሥታት ኤዊን ፥ ሬቄምን ፥ ጹርን ፥ ሑር
ንና ሬባዕን ገደሉ ፤ የቢዖርን ልጅ በለዓምንም
ገደሉት ።
[9]የእስራኤል ሕዝብ ምድያማውያን ሴቶች
ንና ሕፃናትን ማረኩ ፤ የከብት ፥ የበግና የፍየል
መንጋዎቻቸውን ወሰዱ ፤ ሀብታቸውን ሁሉ በዘ
በዙ ፤ [10]ከተሞቻቸውንና የሰፈሩበትን ቦታ

30፡2 ፦ ዘዳ. 23፡21-23 ፤ ማቴ. 5፡33 ።

ሁሉ እቃጠሉ፤ 11 እስረኞችንና እንስሳትን ሳይ
ቀር የማረኩትን ነገር ሁሉ ሰብስበው፥ 12 ከዮር
ዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ ትይዩ በሞአብ ሜዳ ላይ
ሰፍረው ወደነበሩት ወደ ሙሴና ወደ አልዓዛር
እንዲሁም ወደ መላው ማኅበር አመጡአቸው።

### የሠራዊቱ መመለስ

13 ሙሴ፥ አልዓዛርና ሌሎቹም የማኅበሩ
መሪዎች ሠራዊቱን ለመቀበል ከሰፈር ወጡ፤
14 ሙሴ ግን ከጦርነት በተመለሱት በጭፍራ
አለቆች፥ በሻለቆችና በመቶ አለቆች ላይ
ተቈጣ፤ 15 እንዲህም ሲል ጠየቃቸው "ሴቶችን
በሙሉ በሕይወት ያስቀራችሁት ለምንድነው?
16 በፔዖር ሳለን የበለዓምን ምክር ተቀብለው
ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት
እንዲተው ያደረጉ ሴቶች መሆናቸውን ዘነጋች
ሁን? በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የአባር ቸነ
ፈር መቅሠፍት ያመጣም ያ ስሕተት ነበር።
17 ስለዚህ አሁን እያንዳንዱን ወንድ ልጅና እያ
ንዳንዲቱን ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት
የፈጸመች ሴት ግደሉ። 18 ነገር ግን ልጃገረዶ
ቹን ወይም ድንግል የሆኑትን ሴቶች በሕይወት
እንዲኖሩ አድርጋችሁ ለራሳችሁ አስቀሩ።
19 ከእናንተ መካከል ሰው የገደለ ወይም ሬሳ
የነካ ሁሉ ለሰባት ቀን ከሰፈር ውጭ ይቆይ፤
በሦስተኛውና በሰባተኛው ቀን ራሳችሁንና የማ
ረካችኋቸውን ሴቶች፥ 20 እንዲሁም ማንኛው
ንም ልብስ ወይም ከቆዳ፥ ከፍየል ጠጕር
ወይም ከእንጨት የተሠራ ነገር ሁሉ አንጹ።"
21 ካህኑ አልዓዛር ከዘመቻ ለተመለሱት ወን
ዶች እንዲህ አለ፥ "እግዚአብሔር ለሙሴ የሰ
ጠው የሥርዓት መመሪያዎች እነዚህ ናቸው፦
22-23 እንደ ወርቅ፥ ብር፥ ነሐስ፥ ብረት፥
ቈርቈሮ ወይም እርሳስ የመሳሰሉ እሳት
የማይጐዳቸው ነገሮች በእሳት ውስጥ አልፈው
መጥራት ይኖርባቸዋል፤ በኋላም እነዚህ ነገሮ
ችና ሌላው ነገር ሁሉ የሚነጻው ለመንጻት
ሥርዓት በተመደበው ውሃ ነው። 24 በሰባተ
ኛው ቀን ልብሳችሁን ታጥባላችሁ፤ ከዚያም
በኋላ በሥርዓት የነጻችሁ ስለምትሆኑ ወደ
ሰፈር መግባት ይፈቀድላችኋል።"

### የምርኮ ክፍያ

25 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፥
26 "አንተና አልዓዛር ከቀሩት የማኅበሩ መሪ
ዎች ጋር በመሆን እስረኞችንና እንስሳትን
ጭምር በምርኮ የተገኘውን ማንኛውንም ነገር
ቍጠሩ። 27 በሁለት መድባችሁም አንደኛውን
ክፍል ወደ ጦርነት ለሄዱ ወታደሮች፥ ሁለተኛ
ውን ክፍል ለቀሩት የማኅበሩ አባላት ስጡ።
28 ለወታደሮቹ ከተመደበው ክፍል፥ ከአምስት
መቶ እስረኞች አንዱን፥ እንዲሁም ከከብቱ፥
ከአህዮቹ፥ ከበጎቹና ከፍየሎቹ ከአምስት
መቶው አንዱን እጅ ለእግዚአብሔር መባ አድ
ርጋችሁ ለዩ፤ 29 ለእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ
በማድረግም ለካህኑ ለአልዓዛር ስጡት። 30 ለቀ
ሩት የማኅበሩ አባላት ከተሰጠውም ክፍል ከኀ
ምሳ እስረኞች አንዱን፥ በዚሁ መጠን ከከ
ብቱ፥ ከአህዮቹ፥ ከበጎቹና ከፍየሎቹ ለይታ
ችሁ እግዚአብሔር ለሚመለክበት ድንኳን ኀላ
ፊዎች ለሆኑት ሌዋውያን ስጡ።" 31 ሙሴና
አልዓዛርም እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ አደ
ረጉ።
32-35 ለራሳቸው ካስቀሩት ጭምር ወታደ
ሮቹ የማረኩት ንብረት ዝርዝር የሚከተለው
ነው፦ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺ በጎችና
ፍየሎች፥ ሰባ ሁለት ሺ ከብቶች፥ ስልሳ አንድ
ሺ አህዮችና፥ ሠላሳ ሁለት ሺ ደናግል። 36 ለወ
ታደሮቹ ድርሻ ሆኖ የተከፈለው፦ ሦስት መቶ
ሠላሳ ሰባት ሺ አምስት መቶ በጎችና ፍየሎች
ሲሆኑ፥ 37 ከእነዚህም ስድስት መቶ ሰባ አም
ስቱ ለእግዚአብሔር መባ ሆነው የተሰጡ
ነበሩ፤ 38 ለወታደሮቹ የተሰጡት ከብቶች ብዛት
ሠላሳ ስድስት ሺ ሲሆን ከእነርሱም ሰባ ሁለቱ
ለእግዚአብሔር መባ ሆነው የተሰጡ ነበሩ፤
39 ለወታደሮቹ የተሰጡት አህዮች ሠላሳ ሺ አም
ስት መቶ ሲሆኑ ከእነዚህም ስልሳ አንዱ ለእግ
ዚአብሔር መባ ሆነው የተሰጡ ነበሩ፤ 40 ለወ
ታደሮቹ የተሰጡት ደናግል ዐሥራ ስድስት ሺ
ሲሆኑ፥ ከእነዚህም ሠላሳ ሁለቱ ለእግዚአብ
ሔር አገልግሎት የተለዩ ነበሩ። 41 ስለዚህም
ሙሴ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት መባውን
ለእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ በማድረግ ለአልዓዛር
ሰጠው።
42 የማኅበሩ አባሎች ድርሻ ከወታደሮቹ
ድርሻ ጋር ተመሳሳይና እኩል ነበር፤ 43 ይኸ
ውም ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ሺ አምስት መቶ
በጎችና ፍየሎች፥ 44 ሠላሳ ስድስት ሺ ከብ
ቶች፥ 45 ሠላሳ ሺ አምስት መቶ አህዮችና፥
46 ዐሥራ ስድስት ሺ ደናግል ነበሩ። 47 ከዚህም
ድርሻ ሙሴ ከኀምሳው አንድ እስረኛ፥ ከኀም
ሳው አንድ እንስሳ ወስዶ እግዚአብሔር ባዘዘው
መሠረት በእግዚአብሔር ድንኳን ላይ ኀላፊነት
ላላቸው ለሌዋውያን ሰጠ።
48 ከዚህ በኋላ የሠራዊቱ አዛዦች የነበሩት
የጦር ሹማምንት ወደ ሙሴ ቀርበው እንዲህ
አሉ፥ 49 "ጌታ! በእኛ ትእዛዝ ሥር የነበሩትን
ወታደሮች ሁሉ ቈጥረናል፤ ከእነርሱ አንድም
የጐደለ የለም። 50 ስለዚህ እያንዳንዳችን ወስደ
ነው የነበረውን የወርቅ ጌጣጌጥ ማለትም የእ
ግር አልቦውን፥ የእጅ አንባሩን፥ የጣት ቀለበ
ቱን፥ የጆሮ ጕትቻውንና የአንገት ድሪውን

---

31፥16 ፦ ዘኍ. 25፥1-9 ።

ተራራ አጠገብ የሚገኘው የዐባሪም ተራራና ፥
ከዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ ትይዩ በቤትየሺሞ
ትና በሺጢም ሸለቆ መካከል ያለው የሞአብ
ሜዳ ።

### እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከመሻገራቸው በፊት የተሰጣቸው መመሪያ

[50] በኢያሪኮ ትይዩ ከዮርዳኖስ ማዶ በሞአብ
ሜዳ ላይ ሳሉ ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸው
ዘንድ እግዚአብሔር ለሙሴ የሚከተለውን
መመሪያ ሰጠው ፤ [51] “ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ
ወደ ከነዓን ምድር ስትገቡ ፥ [52] በምድሪቱ ላይ
የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ከፊታችሁ ንቃቅላችሁ
አባርሩ ፤ ከድንጋይና ከብረት የተሠሩትን ጣዖቶ
ቻቸውን እንዲሁም የማምለኪያ አጸዶቻቸውን
ሁሉ በማፈራረስ ደምስሱ ። [53] ለእናንተ
የሰጠኋት ስለሆነ ፥ ምድሪቱን ወርሳችሁ በእር
ስዋ ኑሩ ። [54] ምድሪቱንም በተለያዩት ነገዶችና
ጐሳዎች መካከል በዕጣ ተከፋፈሉ ፤ የጐሳው
ቊጥር ከፍ ላለው ሰፊ መሬት ይሰጠው ፤ የጐ
ሳው ቊጥር አነስተኛ ለሆነው ደግሞ ተመጣ
ጣኝ መሬት ይሰጠው ። [55] በምድሪቱ ላይ የሚ
ኖሩትን ሰዎች ሁሉ አሳዳችሁ ካላጠፋችሁ ግን
ለዐይናችሁ እንደ ስንጥር ለጐናችሁም እንደ
እሾኽ በመሆን ያስቸግራችኋል ፤ በምትቀመጡ
ባትም ምድር ዘወትር ጦርነት በማስነሣት ያስ
ጨንቁአችኋል ። [56] እነርሱን አሳዳችሁ ካላጠፋ
ችሁ እነርሱን ለማጥፋት እንዳቀድሁት ሁሉ
እናንተን አጠፋለሁ ።”

## ምዕራፍ 34
### የምድሪቱ አዋሳኞዎች

[1] እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
[2] “እስራኤላውያንን እንዲህ ብለህ እዘዝ ፦ እኔ
ወደምሰጣችሁ ወደ ከነዓን ምድር በምትገቡ
በት ጊዜ የግዛታችሁ ወሰን እንደሚከተለው
ይሆናል ፦ [3] የደቡብ ድንበር ከጺን ምድረ በዳ
ተነሥቶ የኤዶምን ጠረፍ እያዋሰነ ያልፋል ፤
ይኸውም በስተ ምሥራቅ በኩል የሚጀምረው
ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ ጫፍ ላይ ነው ።
[4] ከዚያም ወደ ዐቅራቢም መተላለፊያ ወደ
ደቡብ በማምራት በጺን አልፎ እስከ ቃዴስ
በርኔ ይደርሳል ፤ ከዚያም በሐጻርአዳር ሰሜናዊ
ምዕራብ አልፎ እስከ ዓጽሞን ይደርሳል ። [5] በግ
ብጽ አዋሳኝ የሚገኘውን ሸለቆ በመዞር በሜድ
ትራኒያን ባሕር ይቆማል ።
[6] “ ‘የምዕራቡ ወሰን የሜድትራኒያን ባሕር
ይሆናል ።
[7] “የሰሜኑ ወሰን የሜድትራኒያንን ባሕር
በመከተል ወደ ሆር ተራራ አልፎ ፥ [8] እስከ
ሐማት መተላለፊያ ይደርሳል ፤ ወደ ጸዳድና ፥
[9] ወደ ዚፍሮን ከተሻገረም በኋላ በሐጻርዔናን
ይቆማል ።
[10] “የምሥራቁ ወሰን ከሐጻርዔናን እስከ
ሸፋም ያለውን መስመር ይከተላል ። [11] ከዚያም
በደቡብ በኩል በዐይን በስተ ምሥራቅ እስካ
ለው ሃርቤልና በገሊላ ባሕር በስተምሥራቅ
ወዳሉት ኮረብታዎች ይዘልቃል ፥ [12] ከዚያም
በስተ ደቡብ የዮርዳኖስን ወንዝ በመከተል ወደ
ሙት ባሕር ይደርሳል ።
“እንግዲህ እነዚህ በአራቱም አቅጣጫ
ያሉት የምድራችሁ አዋሳኞች ይሆናሉ ።”
[13] ስለዚህ ሙሴ ለእስራኤላውያን እንዲህ
አላቸው ፥ “እንግዲህ እግዚአብሔር ለዘጠኙ
ነገድ ተኩል የመደበላችሁና ዕጣ በመጣል የም
ትከፋፈሉት ምድር ይህ ነው ። [14] የሮቤልና
የጋድ ነገዶች እንዲሁም የምናሴ ነገድ እኩ
ሌታ የሆኑት በየቤተሰባቸው በመከፋፈል ፥
[15] በኢያሪኮ ትይዩ ከዮርዳኖስ ማዶ በስተምሥ
ራቅ ርስት ወስደዋል ።”

### ምድሪቱን ለማከፋፈል ኀላፊነት የተሰጣቸው መሪዎች

[16] እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፥
[17] “ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ ምድሪ
ቱን በሕዝቡ መካከል ያከፋፍሉ ፤ [18] እነርሱን
ይረዱ ዘንድ አንዳንድ መሪ ከየነገዱ ምረጥ ።”
[19-28] እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች የሚከ
ተሉት ናቸው ፦

| ነገድ | መሪ |
|---|---|
| የይሁዳ | የዮፎኔ ልጅ ካሌብ |
| የስምዖን | የዓሚሁድ ልጅ ሽሉሚኤል |
| የብንያም | የኪስሎን ልጅ ኤሊዳድ |
| የዳን | የዮግሊ ልጅ ቡቂ |
| የምናሴ | የኤፉድ ልጅ ሐኒኤል |
| የኤፍሬም | የሺፍጣን ልጅ ቀሙኤል |
| የዛብሎን | የፓርናክ ልጅ ኤሊጻፋን |
| የይሳኮር | የዓዛን ልጅ ፓልጢኤል |
| የአሴር | የሸሎሚ ልጅ አሒሁድ |
| የንፍታሌም | የዓሚሁድ ልጅ ፐዳህኤል |

[29] እንግዲህ ለእስራኤል ሕዝብ በከነዓን
ምድር ርስት እንዲያካፍሉ እግዚአብሔር የመረ
ጣቸው ሰዎች እነዚህ ናቸው ።

## ምዕራፍ 35
### ለሌዋውያን የተመደቡ ከተሞች

[1] በኢያሪኮ ትይዩ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ
ባለው በሞአብ ሜዳ ላይ እግዚአብሔር ሙሴን
እንዲህ አለው ። [2] “እስራኤላውያን ድርሻቸው

---

33፥54 ፦ ዘኍ. 26፥54-56 ። 34፥13-15 ፦ ኢያሱ 14፥1-5 ። 35፥1-8 ፦ ኢያሱ 21፥1-42 ።

ከሆን ርስት ለሌዋውያን የሚኖሩባቸውን ከተሞ
ችንና በከተሞቹም ዙሪያ የግጦሽ መሬት እንዲ
ሰጡአቸው ንገር ። 3እነዚህም ከተሞች የሌዋው
ያን ይዞታ ሆነው እነርሱ ይኖሩባቸዋል ፤ የግ
ጦሽ መሬቱም ለከብቶቻቸውና ለሌሎች እንስሶ
ቻቸው ይሆናል ። 4የግጦሽ መሬቱ ከከተማው
ቅጽር ግንብ በሁሉ አቅጣጫ እስከ አራት መቶ
ኀምሳ ሜትር ይርቃል ። 5በዚህም ዐይነት ከተ
ማው በመካከል ሆኖ በአራቱም አቅጣጫ ከማእ
ዘን እስከ ማእዘን የሚኖረው ርቀት ዘጠኝ መቶ
ሜትር ይሆናል ። 6ማናቸውም ሰው ፣ በስሕ
ተት ሰውን ቢገድል ሸሽቶ የሚጠጋባቸው ስድ
ስት ከተሞችን ለሌዋውያን ትሰጣላችሁ ፤ በተ
ጨማሪም አርባ ሁለት ከተሞችን ፣ 7ከነ ግጦሽ
መሬታቸው ትሰጣላችሁ ፤ በዚህም ዐይነት በአ
ጠቃላይ አርባ ስምንት ከተሞች ይኖራቸዋል ።
8በእያንዳንዱ ነገድ ለሌዋውያን የሚመደቡት
ከተሞች ብዛት የሚወሰነው በግዛቱ ስፋት
መጠን ይሆናል ።”

### የመጠጊያ ከተሞች
(ዘዳ. 19፥1-13፤ ኢያሱ 20፥1-9)

9እግዚአብሔር ሙሴን ፣ 10ለእስራኤል
ሕዝብ እንዲህ ብሎ እንዲነግር አዘዘው ፣ “የዮ
ርዳኖስን ወንዝ ተሻግራችሁ ወደ ከነዓን ምድር
ስትገቡ ፣ 11አንድ ሰው ባለማወቅ ተሳስቶ ሰው
ቢገድል አምልጦ የሚደበቅበት የመጠጊያ ከተ
ሞችን ትመርጣላችሁ ። 12በዚያም የበቀል እር
ምጃ ለመውሰድ ከሚፈልግ ከሟቹ ዘመድ ሊሰ
ወር ይችላል ፤ በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው
ለፍርድ ሳይቀርብ መገደል የለበትም ፤ 13ስድ
ስት ከተሞችን ምረጡ ፤ 14ከእነርሱም ሦስቱ
ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ፣ ሦስቱ ደግሞ
በከነዓን ምድር ይሁኑ ፤ 15እነርሱም ለእስራኤላ
ውያንና ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው በእስራኤል
ለሚኖሩ የውጭ አገር ስደተኞች የመጠጊያ
ከተሞች ይሆናሉ ፤ ባለማወቅ ተሳስቶ ሰው የሚ
ገድል ማንኛውም ግለሰብ ከእነርሱ ወደ አንዱ
አምልጦ መጠጋት ይችላል ።
16-18“ሆኖም አንድ ሰው ሆን ብሎ በብረት
ወይም በድንጋይ ወይም በእንጨት መሣሪያ
በመጠቀም ሰው ቢገድል ፣ የግድያ ወንጀል ስለ
ፈጸመ መገደል አለበት ። 19የሟቹ ቅርብ
ዘመድ ነፍስ ገዳዩን የመግደል መብት ይኖረ
ዋል ፤ ስለዚህ ባገኘው ጊዜ ሊገድለው ይች
ላል ።
20“አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከመጥላቱ የተ
ነሣ ገፍትሮ በመጣል ወይም አንዳች ነገር
በላዩ በመወርወር ፣ 21ወይም በቡጢ በመም
ታት ቢገድለው የግድያ ወንጀል ስለፈጸመ መገ
ደል አለበት ፤ የሟች ቅርብ ዘመድ ነፍሰ ገዳዩን
የመግደል መብት ይኖረዋል ፤ ስለዚህ ባገኘው
ጊዜ ሊገድለው ይችላል ።
22“ነገር ግን አንድ ሰው ገፍትሮ በመጣ
ልም ሆነ አንዳች ነገር በላዩ በመወርወር ሌላ
ሰው የሚገድለው ከጥላቻ የተነሣ ሳይሆን በድን
ገት ተሳስቶ ይሆናል ፤ 23ወይም አንድ ሰው
ድንጋይ ወርውሮ ሊጎዳው ያልፈለገውንና ጠላ
ቱም ያልሆነውን ሰው ሳያይ ይገድለው ይሆ
ናል ፤ 24እንዲህ ያለው ሁኔታ በሚፈጸምበት
ጊዜ ማኅበሩ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ለሚፈ
ልገው ለገዳዩ ዘመድ ሳይሆን ለራሱ ለገዳዩ
መፍረድ ይኖርበታል ። 25ማኅበሩ በግድያ ወን
ጀል የተከሰሰውን ሰው ከሟች ዘመድ እጅ በመ
ታደግ አምልጦ ወደነበረበት ወደ መጠጊያ ከተ
ማዋ መመለስ አለበት ፤ በዘመኑ ሊቀ ካህናት
የሆነው ሰው እስከሚሞትበት ድረስ እዚያው
መቆየት ይኖርበታል ። 26በግድያ ወንጀል የተከ
ሰሰው ሰው አምልጦ ከተጠጋበት ከተማ ለቅቆ
ከሄደና ፣ 27የሟች ዘመድ አግኝቶ ከገደለው
የዚህ ዐይነቱ የበቀል እርምጃ በነፍሰ ገዳይነት
አያስጠይቅም ። 28ምክንያቱም በግድያ ወንጀል
የተከሰሰው ሰው ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት ድረስ
በዚያው በመጠጊያ ከተማ መቈየት አለበት ፤
ከዚያ በኋላ ግን ወደ ቤቱ መመለስ ይችላል ፤
29ይህ ሕግ በምትኖሩበት አገር ሁሉ ለእናን
ተና ለዘሮቻችሁ መመሪያ ይሆናል ።
30“በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ማንኛውም
ሰው የሞት ፍርድ ሊበየንበት የሚችለው ሁለት
ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች የመሰከሩበት
እንደሆነ ነው ፤ የአንድ ሰው ምስክርነት ግን ለግ
ድያ ወንጀል የተከሰሰውን ሰው ሊያስጠይቀው
አይችልም ። 31ማንኛውም ነፍሰ ገዳይ በሞት
መቀጣት አለበት ፤ ገንዘብ በመክፈል ከዚህ
ቅጣት ሊያመልጥ አይችልም ። 32አንድ ሰው
ወደ መጠጊያ ከተማ ሸሽቶ ቢያመልጥ ሊቀ ካህ
ናቱ ከመሞቱ በፊት ወደ ቤቱ መመለስ ይችል
ዘንድ ገንዘብ እንዲከፍል አትፍቀዱለት ።
33ይህን ብታደርጉ የምትኖሩበትን ምድር ታረክ
ሳላችሁ ፤ የነፍስ ግድያ ወንጀል ምድሪቱን ያረክ
ሳል ፤ ስለዚህ የነፍሰ ገዳዩ ደም ካልፈሰሰ በቀር
ምድሪቱን ከደም ለማንጻት የሚፈጸም ሌላ ሥር
ዓት የለም ። 34እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ስለሆንሁና በእስራኤል ሕዝብም መካከል ስለም
ኖር የምትኖሩበትን ምድር አታርክሱ ።”

## ምዕራፍ 36
### ላገቡ ሴቶች የተመደበ ርስት

1የዮሴፍ ልጅ ምናሴ የወለደው የማኪር
ልጅ የገለዓድ ጐሳ የሆኑት የቤተሰብ አለቆች
ወደ ሙሴና ወደ ሌሎቹም መሪዎች ቀርበው
እንዲህ አሉ ፤ 2“ምድሪቱን በዕጣ ለእስራኤል

35፥30 ፦ ዘዳ. 17፥6 ፤ 19፥15 ። 36፥2 ፦ ዘኍ. 27፥7 ።

